የሰ/መ/ቁ 88135

ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አምልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - ነ/ፈጅ ወርቅነህ ዘውዱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነፃነት ሀቤቤ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፤

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተሸከርካሪ የሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የተሰጠ የመድን ሽፋን ኃላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡ ከስር ፍርድ ቤት በዚህ ክርክር ወ/ሮ አለምነሽ ገብረ ማርያም በራሷና ሞግዚት በሆነችላቸው እነ ህፃን አዲስ ብርሃኑ(አራት ሕፃናት) ስም ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ደግሞ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም በተጠሪ ላይ ያስቀረበችው ክስ ነው ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም የተጠሪ ንብረት ቁጥር 3-178887 የሆነ መኪና የልጆች አባት የሆነውን አቶ ብርሃኑ ጥላሁንን የግጭት ጉዳት አድርሶበታል ባለቤቴና የልጆቼ አባት በአደጋው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ስለሞተ በእኔና ልጆቹ በመተዳደሪያ እረገድ ለደረሰብን ጉዳት ብር 541,538 (አምስት መቶ አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር) ካሳ እንዲከፈል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ የተጠየቀውን የካሳ መጠን በመቃወም ክርክር ያቀረበች ሲሆን አመልካች የመድን ሽፋን

የሰጠ በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ እንዲሰጥላት ጠይቃለች አመልካች በክርክሩ ገብቶ የተጠሪ መኪና በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ለአንድ ሰው እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን ከገለፀ በኃላ ተጠሪ በመድን ታሳቢ መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን የማሳወቅ ግዴታዋን አልተወጣችም፡፡ ስለዚህ በመድን ውሉ መሰረት ሽፋን እንድሰጥ አልገደድም፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ለወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያና ልጆቻቸው ብር 222,538 ወይም /ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት እንድትከፍል ወስኗል፡፡ ከዚህ የካሳ ገንዘብ አመልካች ብር 40.000 (አርባ ሺህ) እንዲከፍል ወስኗል፡፡

2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአስር ቀን ውስጥ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ በመድን ውሉ ገብታለች፡፡ ተጠሪ በ10 ቀን ውስጥ አደጋ የደረሰ መሆኑን ያላሳወቀች በመሆኑ አመልካች በመድን ውል መሠረት ብር 40.00 የመክፍል ግዴታ የለበትም የበታች ፍርድ ቤቶች በግልፅ የተቀመጠውን የውል ቃል በመተላለፍ አመልካች በመድን ውል መሠረት ኪሳራውን እንዲጋራ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
3. ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈው መልስ ተጠሪ በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ለአመልካች አለማሳወቁ አመልካች በመድን ውል መሰረት ለሶስተኛ ወገኖች የመድን ሽፋን የሰጠበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነቱን አያስቀርም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፤
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት የመለያ ቁጥር 3-17887 የሆነችው መኪና በሚች ብርሃን ጥላሁን ላይ ባደረሰው የሞት እደጋ ተጠሪ ከተወሰነባት የካሳ ገንዘብ ውስጥ አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ለሚች አቶ ብርሃን ጥላሁን ሚስትና ልጆች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪ መኪና በሌላ ሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ለሚያደርሰው አደጋ እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ኃላፊነቱን ለመጋራት የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት መኪና በሚች ብርሃን ጥላሁን ላይ የሞት አደጋ ማስከተሏና ተጠሪ ለጉዳቷ ኃላፊ መሆኗ በፍርድ ቤት ውሳኔ

ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሚከራከረው በሰጠሁት የመድን ሽፋን መሰረት ገንዘቡን ለከሳሾች የምከፍለው ተጠሪ በመድን ውሉ መሰረት በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ብታሳውቀኝና ግዴታዋን ብትወጣ ነበር፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታዋን ያልተወጣችና በአስር ቀን ውስጥ አደጋው መድረሱን ያላሳወቀችው በመሆኑ የመድን ሽፋን የሰጠሁበትን ገንዘብ ለከሳሾች የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአሰር ቀን ውስጥ ለአመልካች ለማሳወቅ የውል ግዴታ የገባች መሆኑን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የምትከራከረው እኔና አመልካች በቅድመ ሁኔታነት በመድን ውል የተዋዋልነው ሃይለ ቃል በህግ ያልተፈቀደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ነው፡፡

6. ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ተደንግጓል፡፡ የመድን ሥራ የሚሰሩ የመድን ኩባንያዎች በመድን ፖሊሲ ውስጥ ፖሊሲውን ተጠያቂነትን አያስከትልም ወይም በፖሊሲው መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሆነው ክስተት ከደረሰ በኃላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ሳይፈጸም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል የውል ሁኔታ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና የወጣው አዋጅ ቁጥር 559/2000 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ አደጋው ከደረሰ በኃላ በአስር ቀን ውስጥ ካላሳወቀችኝ በመድን ፖሊሲው መሰረት ገንዘቡን ለተጎጂዋ (ለከሳሾች) የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ ይዘቱ የተገለፀውን የህግ ድንጋጌ የሚጥስና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች በመድን ፖሊሲው መሠረት ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ብር ለከሳሾች እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ